# ሰላም ለተዋሕዶ እምነት፣ ሰላም ለእምነቱ ተከታዮች

በመጀመሪያ የጠራ እምነትና ቃልን መሠረት ማድረግ ይገባል፡፡ ስለ እምነት ስንናገር የቁልምጥ ቃላትን ልንጠቀም አይገባም፡፡ ዘወትር የክርስቶስ ትምህርት 4ቱ ወንጌላትን ማንበብ ገባል፡፡ ፈሪሳዊያንና ሰዱቃዊያን በስሕተት ሲዳፈሩት ክርስቶስ ኃይለ ቃል ያለበትን መልስና ትምህርት ያቀርብ ነበር፡ ፡

በቴክሳስ የተደረገው ጉባኤ እንደ እምነት ወግ የዘገየ ቢሆንም ሙከራው መልካም ነበር፡፡ መሠረተ ይዘቱ ስንመረምር ግን የተጣላች ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፡ አንድ ናትና፡፡ የተጣላ እምነት አይደለም፡፡ እምነት ወይም አምላክ አንድ ነውና፡፡ እኔ ልሾም እኔ ልበልጽግ የተጣሉ መነኮሳት ናቸው እንጂ፡፡ ህዝበ ክርስቲያኑ በማያውቀው ምሥጢር እርስ በራሱ ተለይቶ ይኖራል፡፡ ምንኩስና ሥርዓት ለሥልጣኑ ሲል በሚፈጥረው ሰበብ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ህዝበ ክርስቲያኑ ሲጨፋጨፍ ሲጣላ ኖሮአል፡፡ እንዲህ ሊሆን የቻለውም የምንኩስና ሥርዓት ያለ ታሪኩ፡ ያለ መደቡ፡ ያለ ቦታው፡ ያለ ውሉና……የመሳሰሉትን ሁሉ ረግጦ ከቤተ ክርስቲያንዋ ቁንጮ ወጥቶ ስለ ተከመረ ነው፡፡ አሁንም የሚነታረኩ ለራሳቸው ሥልጣን እነጂ ለቤተ ክርስቲያን ክብርና ለምእመናን አንድነት እንዳይደለ በድርድራቸው ጓደት ማወቅ ይቻላል፡፡ መነኩሴና መነኩሴ ተደራድረው የሚፈይዱት ውጤት እንደ ማይኖር አስቀድሞ ማወቅም ብልህነት ነው፡፡ ለዚህ መድኀኒቱ ሌላ ነው፡፡ እሱም ሊቃውንት፡ ካህናትና ህዝበ ክርስቲያን አንድ ኃይል ፈጥረው መሠረተ ሕግ ካልጣሉበት በቀር እየተድበለበሉ፡ ህዝበ ክርስቲያኑን እያሳዘኑና ለነጣቂዎች እያዘረፉ መኖር ነው፡፡

## አቡነ መልከጼዴቅ ማን ናቸው?

በኢትዮጵያ ኪነ ጽሑፍ ሥርዓት ጽሑፌ ቦታ እንዳያጣ የቀድሞ የክብር ስማቸውን አስቀምጬ አለሁ፡፡ የተዋሕዶ እምነትና የንጉሡም ክብደት ተጨምሮበት ሊሆን ይችላል፡ አንድነትዋንና ክብሯን ሊጠብቁላት የመጨረሻው የክብር ቦታዋ አንድ ደረጃ በቀረው ላይ ሰየመቻቸው፡ አከበረቻቸው፡፡ ይሁን እንጂ አገር ውስጥ ሳሉም ለግላቸው ይጠቀሙባት እንደ ነበሩና ለተዋሕዶ እምነት አስተዳደር የማታዘዙ እንደ ነነበሩ ሕይወት ታሪካቸውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አሁንም ውጪ ሀገር ኄደው ከመጀመሪያ ግንጠላው ጀምሮ የግንጠላው ተጠያቂ እሳቸው ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለክብራቸው ለኑሮአቸው ሲሉ ቤተ ክርስቲያንዋን የከፈሏት እሰቸው ናቸው፡፡ አቡነ መርቆሬዎስ በፍጹም በዚህ ጉደይ ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ግንጠላው ሲከናወን አልነበሩምና፡፡ አገር ውስጥ ነው የነበሩ፡፡ ኋላ ከጥቁሩ ባሕር ኄደው ተቀላቀሉ እንጂ፡፡ አቡነ ይስሐቅም በእሳቸው ተገፋፍተው ፈጸሙት እንጂ አላሰቡበትም ነበር፡፡

ወደ መሠረታዊ አጭር ታሪክ ልግባ፡፡ በ1983 ዓ. ም. የውጪው ተደራዳሪ ሲኖዶስ ነኝ የሚለው ሲገነጠል በመጀመሪያ የዘመኑ ምስክር እኔ ራሴ መሆኔን ማስቀደም ይገባል፡፡ ሐምሌ ወር 28 ቀን ሐሙስ ይመስለኛል ኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ ሰሚናሪ (ኮለጅ) ከሚባል ቦታ ስብሰባ ተጀመረ፡፡ በየዓመቱ የአሜሪካ ርክበ ካህናት በአቡነ ይስሐቅ መሪነት ስንሰበሰብ ነበርንና ነው፡፡ በየዓመቱ የማይቀሩ የነበሩ በጣም የሚመለከታቸው ካህናት ቄስ አስተርአየ ጽጌና መምህር ፍሥሐ ጽዮን ካሣ የሚባሉ የዋሺንግቶን ደሰ. ኑዋሪዎች ኢንፎርሜሽን ሳይኖራቸው አይቀርም አንኄድም ብለው ቀሩ፡፡ እኔ ግን ከሥራየ ያለ ክፍያ የሳምንት ፈቃድ ወስጄ ከዋሸንግቶን ዲሲ ወደ ኒው ዮርክ ከተማ ኄድኩ፡፡

ስብሰባው የተጀመረው ሐሙስ ቀን ነበር፡፡ ከሐሙስ እስከ ቅዳሜ ስብሰባው ሲከሃኄድ ተሠውሮብኝ ነው መሰለኝ ምንም የሰማሁት ነገር አልነበረም፡፡ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ከኢትዮጵያ ሲኖዶስ እንገነጠል አለን የሚል ሐዲስ ሐሣብ ሰማሁ፡፡ ሀላፊነቱ የአቡነ ይስሐቅ የነበረ ቢሆንም ተገንጣይ ስብሰባውን የመሩት ሊቀ ጳጳስ መልከጼዴቅ ነበሩ፡፡ ለግንጠላው ትልቅ ምክንያት ሆኖ የቀረበውም አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ ሆነው ከኢትዮጵያ ሲኖዶስ ኅብረት አይኖረንም ነበር፡፡ ከዚህ ችግር የደርሰው የሰሜን አሜሪካ፡ የደቡብ አመሪካና የኢሮፐ ሀላፊ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ይስሐቅ ሳያስቡትና ሳይፈልጉት በአቡነ መልከጼዴቅ ግፊት ግንጠላው ተፈጽሞአል፡፡ እኛ ራሳችን ጠንቅቀን የምናውቀው ቢሆንም ኋላ ራሳቸው አቡነ ይስሐቅ ሳላስበው አሳስተውኛል ብለዋል፡፡ በመጀመሪያ በዚሁ ግንጠላ የተቃወሙት 1ኛ. አባ ሐዲስ ግደይ 2ኛ. ስም ዘነጋሁ የቤርሙዳ ተወካይ ካህን፡፡ 3ኛ. ታናሹ አባይስሐቅ ከሚኒሶታ የመጡ፡፡ 4ኛ. እኔ ራሴ ነበርን፡፡ ደጋፊዎች፡ 1ኛ አቡነ ይስሐቅ 2ኛ. ሊቀ ጳጳስ መልከጼዴቅ፡፡ 3ኛ. ሊቀ ካህናት ምሳሌ ከካናዳ፡፡ 4ኛ. ቄስ ከበደ ከምዕራብ ስቴቶች፡፡ 5ኛ. ስማቸውን የረሳሁት ሌላዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት 5ኛው ፓትርያርክ እንዲመረጥ በቅድሚያ ኢትዮጵያ ውስጥ ተስማምተው ፈርመዋል፡፡

ግንጠላው ሲፈጸም አቡነ መርቆሬዎስ አገር ቤት ስለ ነበሩ የግንጠላው መሪ ወይም ተባባሪ ሊባሉ አይገባም፡፡ ኋላ በጊደቱ ክስተት የተገኙ ናቸው፡፡ እሑድ የሰንበት አገልግሎት አድርሰን ዕረፍት ነበር፡፡ ሰኞ ከአባ ሐዲስ በስተቀር ሁሉም በመገንጠሉ ተስማምተዋል፡፡ ሰኞ ጧት ስብሰባው እንደ ቀጠለ፡ ወደ 5፡50 ገደማ በአቡነ ይስሐቅ ጠሪነት የኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጠኛ መጣ፡፡ በመጀመሪያ አቡነ ይስሐቅን አነጋገረ፡፡ አቡነ ይስሐቅ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ በእምነት ሳይሆን በአስተደደር ከኢትዮጵያ ሲኖዶስ ተገንጥለናል አሉ፡፡ ለኢትዮጵያ ሲኖዶስ አንታዘዝም በማለት መግለጫቸውን ሰጡ፡፡ በመቀጠል እያንዳንዱን ተሰብሳቢ ከጠየቀ በኋላ ጋዜጠኛው ተሰናብቶ ኄደ፡፡ ከዚያ ምሳ በላንና የሰዓት በኋላ ስብሰባው

ቀጠለ፡፡ ስብሰባው ሲጀመር ተነሣሁና የእውነት የሐይማኖት ሥራ መስሎኝ ሥራዬን ትቼ መጥቼ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ወደ አልሆነ አቅጣጫ ስለ አመራ ከእምነቴና ከፍላጎቴ ጋር እንደ ማይስማማ አረጋግጬ አለሁ፡፡ ስለ ሆነም ከዚቺ ደቂቃ ጀምሮ ከአናንተ ጋር ኅብረት አይኖረኝም በማለት ስብሰባውን ረግጬ ወጣሁ፡፡ ከጸሎታቸውና ስብሰባቸውም ኅብረት ኖሮኝ አያውቅም፡፡ ችግር ስለ ሆነ በለቅሶ ጊዜ ብቻ እንገናኝ ነበርን፡፡ አንድም የተዋሕዶ እምነት ባለሥልጣን ሳይሰማ በመጀመሪያ ግንጠላውን የተቃወምኩት እኔ ራሴ ነኝ፡፡ ሁለተኛ አባ ሐዲስ እንደ ተቃወሙ ስብሰባውን ጨርሰው ኄደዋል፡፡ አባ ሐዲስ ይህን በመፈጸማቸው የአቡነ ጳውሎስ ባለ ውለታ ሆነው ዘልቀዋል፡፡ ከላይ ካልተፈቀደ፡ በመንፈስ ቅዱስ ካልተላከ ሊሆን ኤችልምና ባይሳካም ለጵጵስናም ተመልምለው ነበር፡፡ በሁለቱም ወገን ተወጋግዘው እያሉ የሁለቱም ቦታ መነኮሳት አብረው ይቀድሱ እንደ ነበሩ ብዙ ምእመናን ያውቃሉ፡፡ የምንኩስና ሥርዓት ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ጥበቃ ይልቅ ለራሱ ክብር ለመደቡ ጥንቃቄ እንደ ሚያደርግ በኂደቱ የተረጋገጠ ነውና፡፡

አቡነ መልከጼዴቅ በሥልጣን ላይ እያሉ የአንድነት ሰላም እናያለን ብሎ መጠበቅ ሞኝነት እንደ ሚያስመስል ማወቅ በተገባ ነበር፡፡ ተስፋ የሚያደርጉ ምእመናን ካሉ፡ በውጪው ዓለም በተለይ በሰሜን አሜሪካ ውስጥ ያላቸውን ካፒታልና ክብር ባለ ማወቅ ሊሆን ችላል፡፡ ዐሥራት በኩራት የታዘዘ ቢሆንም በስመ ሕገ አምላክ ለፖለቲካ ክንውን የሚያውሉትን በተለያየ ጊዜ በዓላትን አደረግን በማለት የዋሁ ህዝብን እንዴት እንደ ሚዘርፉት ለመገመት የሚከብድ አይደለም፡፡ ለብዙ ዓመታት ፖሊቲካል ሳይንስን የተማረውን ተመራማሪ ምሁር መነኮሳት እንዴት እንደ ሚያታልሉት ለመገመትም በጣም ከባድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሲኖዶስን ከሚከተል ህዝብ በእጥፍ የነሱ ይበልጣል፡፡ የጸሎት ቤታቸው ዐቅምና ጉልበትም በዚያ ልክ ነው፡፡ እና ተቀናቃኝ በሌው መድረክ ላይ ሆነው በነፃነት ያለ ገደብ ዶላርን እያፈሱ ከሚኖሩበት ዓለም ተነቅለው ወደ ንዝንዝ ይመጣሉ ብሎ መጠበቅ የቀድሞ የአባ ሀብተ ማርያምን የሥራ ልምድ ካለ ማወቅ በላይ መጃጃልም ነው ሊያስብል ችላል፡፡ ከዚያ ያሉ የነሱ አቢያተ ክርስቲያናት (በእምነት አልተገነጠልንም) ስለ አሉ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሲኖዶስ ሥር ይሁን ቢባል ይስማማሉ ብሎ የሚያምን ምእመን የነሱን መደራጀትና አስተሳሰብ ባለ መረዳት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምናልባት አቅጣጫውን ካላበላሸ በቀር ከአንድ ሰው ዕድሜ በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡ በአሜሪካ ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ሲኖዶስን ይከተላል የሚባል ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የአገልጋዩ መነኩሴ ንብረት ነው፡፡ ሀብትነቱ ወይም አካውንቱ በኢትዮጵያ ሲኖዶስ ሥር ይሁን ቢባል በዚሁ የሚስማማ አንድም ካህን አይገኝም፡፡ ሁሉም እንደነ እንቶኔ ይሸፍታል፡፡ ስለ ዚህ ቤተ ክርስቲያንዋ በውጪው ዓለም ወጥ የሆነ ሥርዓት የላትም ቢባል እውነቱን ሊያጎላው ይችላል፡፡

## አቡነ መርቆሬዎስ

አንዳንድ የዋሆችና የደርግን ዘመን ዘመነ ፍዳ ምንም የማያውቁ ንጹሐን ብራናዎች አቡነ መርቆሬዎስ ወደ ፐትርክናው ይመለሱ የሚል መጠይቅ አጥማጆችን አስነብበዋል፡፡ ሞኝና ወረቀት የያዘው አይለቅም እንደ ተባለው (ይህ ሹመት በአንድ ሀገር በአንድ ዘመን ቢሆን ለሁለት ሰው ልትሆን አይገባም፡፡ ይህ ከተደረገ ግን አስቀድሞ ለተሾመው ትፅና) የሚለውን የፍትሐ ነገሥት ጠቅሰው ያላዝናሉ፡፡ በዚህ ዝግጅት አቅራቢው ውሳኔ ግን ይህ ንባብ አቡነ መርቆሬዎስን የማይመለከት ቢሆንም፡ ፍትሐ ነገሥት ግን እንዲህም ይላል፡፡ አማፂ ጳጳስ ከኀዲ ንጉሥ ከተነሡ ህዝቡ ተባብሮ ከሥልጣናቸው ያወርዳቸዋል ይላል፡፡ ወደ ፍሬ ነገሩ እንመለስና የማያስመልሳቸው በዘመኑ የተፈጸሙ እንዲህ ሆነ እንዲህ ተደረገ የሚለውን ትተን ምክንያቱ ብዙ እና ከባድ ስለ ሆነ፡ በቀላሉ ስንመለከተው 1ኛ. በዕድሜ የገፉ ይመስለኛል፡፡ አንድ ሰው ከመነኮሰ ለሥራ የተፈቀደ ባይሆንም ካልሠሩ ከወንበር መቀመጡ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም፡፡ 2ኛ. በአቡነ መልከጼዴቅ አማካሪነት ለሲኖዶስ ማመልከቻ ጽፈው እንደ ወረዱ በአጠገባቸው የነበሩ የሚያረጋግጡት ነገር ነው፡፡ ስለ ሆነም ከ21 ዓመት በኋላ ወደ ወንበር ይመለሱ ማለት በ2000 ዘመን ውስጥ ይህን መሰል የተፈጸመ ታሪክ ይኖራል ተብሎ አይገመትም፡፡ ስሜትም አይሰጥም፡፡ አገራቸውን ገብተው በክብር መሰንበት ግን ተገቢ ሊሆን ይችላል፡ ላገርም ክብር ነውና፡፡ ያውም አቡነ መልከጸዴቅ ከፈቀዱላቸው ነው፡፡

## መፍትሔ

በአሁኑ በዚሁ በተለመደው እየተድበለበለ ይቆይ፡፡ ለረጅም ፕሮገራም ለወደ ፊት ግን፡ ቤተ ክርስቲያንዋን ሊታደጋት የሚችል የሊቃውንት፡ የሕጋዊያን ካህናትና ምእመናን የሆነ ኀይል ተፈጥሮ ካልደረሰላት በቀር መደብ ጠባቂ መነኩሴና መነኩሴ ተደራድሮ የተሻለ ዐቅም ይፈጥርላታል የሚል ተስፋ ከዚሁ ቢዘጋ እውነትነትን ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከተደራረዳሪው ቡድን ውስጥ ንቡረ እድ ኤልያስና ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንደ ሁለተኛ ፍጡር ሆነው የተጠቀሱት ምን ለማለት ነበር? ንቡረ እድ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንደኛው ናቸው፡፡ በዕውቀትና በሥነ ሥርዓት ከማንም በላይ ቤተ ክርስቲያንን ሊወክሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ሊቀ ካህናት ምሳሌም መገንጠላቸውን ሳናስታውስ በሕገ ዘካርያስ የፀኑና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የጠበቁ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሌላዎች ግን እውነቱን እንናገር ከተባለ የክርስቶስና የሓዋርያት ትዕዛዝ አያውቃቸውም ቢባል እውነትነቱን ያረጋግጣል፡፡ በራሳቸው ሥልጣን በራሳቸው ስብሰባ በራሳቸው ውሳኔ ያደጉ ናቸውና ነው፡፡ የክርስቶስና የሐዋርያት ትዕዛዝ የሚጸየፋቸው መሆናቸውን እንዴት አያውቁም? የእምነትዋ አባላት ሁሉ (www.) ይህን ማወቅ ይገባቸዋል፡፡ የእምነት ውሳኔ ሲወሰን፡ በማን ለማን ምን የሚለውን በትክክል መታወቅ አለበት፡፡

የቤተ ክርስቲያንዋ አባለት ሁሉ ልብ በሉ፡፡ የፖለቲካና የግል ተጠቃሚዎች ህዝቡን የሚያወናብዱበት ልዩ ጎራ መፍጠራቸውን አትዘንጉ፡፡ ሳይንስን ሊመራመሩ በቴክኖሎጂ አገርን ሊሳድጉ ከዩኒበርሲቲ ተመርቀው የወጡ፡ ያለ ቦታቸው ተዘፍቀውና ለራሳቸው ተደናግረው ህዝበ ክርስቲያንን ሲደናግሩ የሚታዩ ብዙ ናቸው፡፡ የውጪ ሲኖዶስ የግቢ ሲኖዶስ እያሉ ዐውቀው በእኩልነት እያወዳደሩ የዋህ ህዝበ ክርሰቲያኑን እያመሱት ነው ያሉ፡፡ ለመሆኑ

ስለ ቤተ ክርስቲያንዋ በየፊናው የሚጽፉ ያሉና ህዘቡን የሚያተራምሱት ያሉ እነ ማን ናቸው? ከደጀ ሰላምዋ ከትምህርት ቤትዋ ኁሮ የሰነበቱና ያደጉ ናቸው? በድርጅትና በጓደኛነት እየተሰባሰቡ የሚያምሱአት ባለቤት በመጥፋቱ ነው፡፡ የሚመለከተው ባለ ቤት ሁሉ ጥግ ጥጉን ይዞ ዝም ብሎ ይመለከታቸዋል፡፡ ለመሆኑ የውጪ ሲኖዶስ የግቢ ሲኖዶስ ማለት ምን ማለት ነው፡፡ ከፈለጉ አገራቸው ነው ይምጡ መብታቸውን ይጠቀሙበት፡፡ አለዚያ አሜሪክ የዓለም ህዝብ አገር ነችና የፈለጉትን ጠርተው ከዚያ መኖር እንደ ጀመሩት በዚያው ይግፉበት፡፡ በሀገሩ ውስጥ የሚኖር የኢትዮጵያ ህዝብ በሀገሩ ውስጥ ያለ የነበረ ሲኖዶስ በቀር ሌላ የሚያውቀው ሲኖዶስ ሊኖር አይችልም፡፡

አንድ ትልቅ ዋርካ አለ እንበል፡፡ የዋርካውን ፍሬ እየመጠመጡ ከሚኖሩ ብዙ ዎፎች አምስት ስድስት ዎፎች ተደናግረው ወደ ሌላ ዋርካ ኄደው ቢቀሩ፡ ትልቁ ዋርካ ምን ይጎድልበታል? ፍሬው ልምላሜው እንዳለ ይቀጥላል፡፡ በዚሁ መሠረት ሲመጠምጡአት የነበሩ ንዝንዛቸውን ይዘው ከዚያ ኄደው ቢቀሩ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ዕምነት ምን ይቀርባታል፡፡ በተለይ ውጪ ሀገር ኄደው የሚመለሱ መነኮሳት አስፈላጊ ያልሆነ የተለያየ ፈሊጥ ይዘው ነው የሚመለሱ፡፡ ለምሳሌ፡ እስከ እኛ ዕድሜ ድረስ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ እምነት ትባል የነበረቺቱ ወደ ግሪክ ኄደው ቅይጥ ቴኦሎጂ (ነገረ መለኮት) ሽምተው በሚመጡ መነኮሳት ኦርቶዶክስ የሚል ቅይጥ ሰምንም ይዘው በመምጣታቸው ኦርቶዶክስ እየገነነ ተዋሕዶ እየተዋጠ ካለንበት ደርሰናል፡፡ የእምነታችን ፍጹማዊ ትርጉምም ተዋሐደ ከሚለው የተገኘ ተዋሕዶ ብቻ ነው፡፡ እስከ 60ዎቱ ዓ. ም. ድረስ የሀገር ቤት ሊቃውንት ኦርቶዶክስ የሚባል ቅጽል ስም አያውቁትም ነበር፡፡

በሌላ ወገን ልጅ ኢያሱ የአያታቸው የዓፄ ምንሊክ ዙፋን ይዘው ነገሡ፡፡ ስለ አልቻሉበት ወይም እግዚአብሔር በቃህ ስላላቸውና ለምክንያትም እኅታቸው ስለ ወለደች እኅቴን ልተይቅ በማለት ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር ኄዱ፡፡ የኢትዮጵያ መኳንንት ተሰብስበው መክረው የዓፄ ምንሊክ ሴት ልጅ ንግሥት ዘውዲቱን ከላስታ አምጥተው አነገሡ፡፡ ራስ ተፈሪን አልጋ ወራሽ ብለው ሾሙ፡፡ የልጅ ኢያሱ አባት የወሎ ገዥ የነበሩ ንጉሥ ሚካኤል ንጉሥ ነኝና በማለት ህዝባዊ ከሆነው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ሰገሌ ላይ ጦርነት ገጠሙ፡፡ ግን ግለኛ ንጉሥ ስለ ሆኑ አላሸነፉም፡ ከመንግሥት ጋር ለመወዳደር አልቻሉም፡፡ ልጅ ኢያሱም በዚያው ቀሩ፡፡ አሁንም ከዚያ ኄዶ ራሱ ሲኖዶስ ነኝ ስለ አለ ሁለት ሲኖዶስ እያሉ መጥራት አግባብ ሊሆን አይችልም፡፡ እውነተኛ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ቢሆኑማ መነኮሳት የጻፉት መጽሐፈ መነኮሳት እንደ ሚነበበው ሆሊውድ ከሚገኝበት ወደ ካሊፎርኒያ ከመሰደድ ይልቅ ወደ በረሃ ወደ ጫካ ወደ ገዳም ባመሩ ነበር፡፡ ስለ ዚህ እናንት ጸሐፊያን ሁሉ በቃችሁ ህዝቡን አታውኩት፡፡ እባካችሁ ስለ ፈጣሪ እንዳልላችሁ በጽሑፋችሁ እንደ ተረዳሁት ነጋዴዎችና ቀዳዳ ፈላጊዎች ስለ ሆናችሁ ልትሰሙት አትችሉም በማለት ነው፡፡ ፍላጎታችሁን ለማሳካት፡ ቤተ ክርስቲያናችን ትፈርሳለች ትቀጭጫለች የምትሉ ሁሉ የእምነታችሁ አለ መስተካከል ያመለክታል፡፡ ቤተ ክርስቲያንዋን የሚጎዳ አንድም ፍጡር ሊኖር አይችልም፡፡ ምክንያቱም የመሠረታት ክርስቶስ ተጠቃሚ ሊመለከተው የማይችል እርስዋን የሚጠብቅበት ሥውር ሰፍ አለውና ነው፡፡

አሁንም የ6ኛው ፓትርያርክ አስመራጭ ኮሚቴ መቋቋሙ እንደ ነቃፊዎቹ ሳይሆን አግባብ ያለው ነው፡፡ ትክክለኛ ኂደት ነው፡፡ በዚሁ መሥመሩን ይዞ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ፀሐይ እሰከ ሚወጣ ለድብልብሉ ዘመን የሚመረጥ ርስሰ አበውም ከትምህርት ቤትዋ የሰነበተ፡ ከልጅነት እከ ዕውቀት ባህልዋን ያካበተ፡ ከቅድስትዋና ቅኔ ማኅሌትዋ ያደረ፡ ከደጀ ሰላምዋ ያረፈደ፡ ቋንቋዋን የሚሰማና እምነትዋን ያልቀየጠ መሆን ይገባል፡፡ ዓፄ ኃለ ሥላሴም ብትርክናውን ከግብጽ ለማምጣት ከግብፅ ጋር ሲስማሙና ሲፈራረሙ፡ ከገዳም የሚኖር ፍጹም ባሕታዊ፡ ሀገራዊ ትምህርትን የተማረና ህዝብ የሚወደው ርእሰ አበው እንዲ መረጥ ነበር የተስማሙት፡፡ ደርግ ይህን ዶክዩሜንት አይቶ ነው አቡነ ተክለ ሃይማኖትን kgTre xsemTeto ያስመረጠ፡፡ አሁን ግን ውስጠ አዋቂዎች እንደ ሚሉት በዝግ አንደር ግራውንድ ፐትርክናው ከጳጳሳት እንዳይወጣ ሲኖዶስ ወስኖአል ተብሎ ይነገራል፡፡ maን ነው የወሰነው? እነሱ፡፡ ለማን? ለራሳቸው፡፡ ይገርማል የህዝቡ ዓይነ ልቡና ምን ያህል ቢታወር ነው እንዲህ የሚደረገው? በሌላ ቋንቋና ባህል እንዲሁም እምነት የተበረዘ ርእሰ አበው እናደርጋለን ቢባል የቤተ ከርስቲያንዋን ቋንቋ ስለ ማይሰማና ባህልዋን ስለ ማያውቅ እንደ አለፈው ዘመን ከመሰሎቹ ከመነኮሳት ጋር ብቻ ተግባብቶ ከሊቃውንት፡ ከካህናትና ከምእመናን አለመግባባት ሊፈተር ይችላል፡፡

ከእንግዲህ ወዲህ ሁለት ሲኖዶስ ብሎ የሚጠራ ሁሉ አገሩ ኢትዮጵያንና እምነቱን ያቃለለ እንደ ሚሆን ማወቅ ይገባል፡፡ ነጋዴና ገበሬ እንኳን አዳብሎ አይጠራም፡፡ ገበሬ ገበሬ ነው፡፡ ነጋዴ ነጋዴ ነውና፡፡ እግዚአብሐር ቤቱንና በጎቹን ይጠብቅ፡፡ ለባለ ዋጋ ዋጋውን ይክፈል፡፡

ኪነ ጥበብና ሥነ ጥበብ

ወይም ይትባርከ ገሠሠ፡

E-mail:barekges@yahoo.com